የምፅዓቱ የምሥራች

ቅጽ 83 ቁጥር 2(974)
እና 83 ቁጥር 3(975)

“በፊትህም የሚሄድ እርሱ እግዚአብሔር ነው” (ዘዳግም 31÷8) “ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ” (ገላትያ 2÷10)

ክርስትና ራስን የመካድ ሕይወትና በእግዚአብሔር የመታመን ጉዞ ነው

“ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች” (ማቴዎስ 24÷12)

የዓመፃም ብዛት ፍቅርን የሚያቀዘቅዝባቸው ውስጥ እኛ ቃሉን በእምነት ተቀበልነን የምንኖርበት እንካተትም።

ይልቁንስ ይህ መልእክት ሕይወታችን በእግዚአብሔርና በፍጥረቱ ላይ ያለማመፃችንን እንድንፈትሽ የሚያሳስበን ነው።

በመጨረሻው ዘመን ይከሰታሉ ተብሎ በቅዱስ ቃሉ የተዘረዘሩ ከፋ ጉዳዮች ወደኋላ እንድናፈግፋ ሳይሆን እነዚህ ነገሮች እንዳይኖሩብን የሚያሰጠነቀቁንና የጌታን ምጽአት በቅድስና ከለመፅ በመራቅ እንድንጠብቅ የሚያሳስቡን ናቸው (2ኛ ጢሞ. 3)

ጌታችን እኛን ለሚሞትን የጠራን የእርሱ ምስክሮች እንድንሆን ነው በምስክርነታችንም ከእርሱ ያየነውን በቃሉ የተማርነውን ከእርሱ ሃቀኛ ተከታዮች የምናየውን መልካም ሥራና ቃል እንድንፈጽም ነው። (ሐዋርያት ሥራ 1÷8 ፣ ማቴዎስ 5÷16)

“መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ” (ማቴዎስ 5÷16)

በዚህ ዓለማችን በክፉ ሥራ በለመፅ በተሞላችበት ወቅት የሚገጥሙንን ፈተናዎችና ተግዳሮቶች መመከትና ማሸነፍ የምንችለው በእግዚአብሔር በመታመን ብቻ ነው። ከእርሱ ከጌታ ከእግዚአብሔር አንዳች የሚሳነው የለም (ሉቃስ 1÷37)

ፈተናዎችና መሰናክሎች በእምነታችን በሕይወታችን ሲገጥሙን ከእምነት እንድንፋታ ወደ ዓለም እንድንመለስ ሳይሆን በጌታ ተመክተን እንድንቋቋማቸውና በድል እንድንበቃ እግዚአብሔር ሁሉን የሚያውቅ የፈቀደው ካልሆነ ምንም እንደማይደርስብን እንገንዘብ ሆኖም ግን በስጋ ፈቃዳችን የጌታን ቃል ቅዱስ መንፈሱንና የወገኖችን ምክር ተግሣጽ ጥሰን በሚደርስብን ከፋት መከራ ሀመም ስቃይ ጌታን ልሰናከርር ፈጽሞ አይገባንም በእውነተኛ ንስኃ መመለስና ምህረቱን መጠየቅ አንድ (1 ጴጥሮስ 5÷7፣ ማቴዎስ 19÷26፣ 1 ዮሐንስ 3÷20፣ ኤርሚያስ 32÷17)

እግዚአብሔር በሕይወታችን ከሚገጥሙን ነገሮች ሰዎች ኃይላት ሁሉ የሚበልጥና ማሸነፍ የሚችል ባለሙሉ ሥልጣን ነው።

በሕይወታችን ኪገጥሙን የሚችሉ ጉዳዮችን በፍርሃትና በጭንቀት እንቀበል። እግዚአብሔር ያሳልፈኛል ይረዳኛል ብለን በሁኔታዎች ላይና ቃል እናሙላ በእምነት በጸሎት በጌታ እንሞላ *“እርሱ ባያድነን ለማልክትህን እንዳናመልክ ካቀምነውም ከመርቁ ምስል እንዳንሰግዳት እወቅ” (ዳንኤል 3÷18)*

በገጠሙን ሁኔታዎች መጨነቅ አንዳች ጥቅም አይሰጠንም ምንም ኃይል አያጎናጽፈንም። ስለዚህ በሚገጥሙን ሁኔታዎች ውስጥ በጸሎትና በምስጋና እርሱ የሚያድነን ጌታ እንዳለ በቃሉ እንታመን። *“ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ” (ፊልጵስዩስ 4÷6)*

ሰው በእንጀራ/ምግብ ብቻ እንደሚይኖር ጌታ በቃሉ ያስተማርንን በመታዘዝ በምንም ሁኔታ ብንሆን ቅዱስ ቃሉን ከነፍሳችንና ከአእምሯችን እንመግበው በቃሉ በተመራ ሕይወትም በሙሰጥም በሙጭም ባሉት ዘንድ በተመሰከረለት መንግድ እንድንኖር እንጣር ጌታችን እንማፀነው (ማቴዎስ 4÷4፣ 1 ዮሐንስ 3÷21)

መጭውን ጊዜ እንዴት እንቀበል?

አብርሃም ከወገኖቹ ከዘመዶቹ ተለይቶ በአዲስ ሀገር ሲኖር የጌታን ቃል በመታመን መጭውን ጊዜ በእምነት በመኖር የነገድ አባት ሆኖ እንደ ቃሉም ዘሩ እንደ ምድር አሸዋና እንደ ሰማያት ከዋክብት በዛለት አብርሃምና

ባለቤቱ ሳራ ሳቅ የፈጠረባትን ይስሃቅ በአብራይስጥ መሳቅ የሚል ተመሳሳይ ትርጉም ያለውን እንዳገኘች በሃገራችን በቤተሰባችን በሠፈራችን የሚይቻለው ተችሎ የእግዚአብሔር በረከት እንዲያገኝን ቃሉን ሳንጠራጠር እንድንቀበል ጌታን እንጠይቀው (ኢሳይያስ 50፡10፣ ዘፍጥረት 12፣ 16፡18፣ ወደ አብራውያን 11)

ራስን የመካድና በክርስቶስ የመታመን ሕይወት

"እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ" (ማቴዎስ 16፡24)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል 16ኛ ምዕራፍ ከደቀመዛሙርቱ ያቀረበላቸው ሰዎች ስለሰሙ ልጅ ምን ይላሉ ብሎ የጠየቃቸውን ደቀመዛሙርቱ የሉሎቹን አስተያየት ተናግረው የራሳቸውን የመለሱት መልስ ሙሉጥ ሐዋርያው ጴጥሮስ አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ያለው መልሱን ጌታ ይህን ሲጋና ደም አልገለፀልህም በሰማይ ያለው አባቴ ነው የገለፀልህ ካለው በኋላ በዚህ አለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እመሰርታለሁ ብሎታል (ማቴዎስ 16፡17)

ይህም የክርስትና እምነት መሠረታዊ መግለጫ የሆነና ሰዎች ክርስቶስን የእግዚአብሔር ልጅነት መቀበልና ማመን በዚህ እምነት ላይም የሰዎች ክርስትና እንደሚመሰን ከማስረገጥ ነው።

ጴጥሮስ ይህን ሀያው የተባለ ምስክርነት ከሰጠ በኋላ ጌታችን ስለሚጠብቀው የሰው ዘር ሁሉ ስለሚድንበት የመስቀል መከራና ሞቱ በተናገረበት ወቅት ግን ጴጥሮስ ይህ ከእንቱ ይራቅ በማለት ኪገዳደረው በፈለገ ጊዜ ጌታ ያንን የመስቀል ዘላለማዊ ሥራ የሚገዳደረውን ሰይጣንን መገሰፁ ይታወቃል። ከተግሳፁም በኋላ የክርስትና ልዩ ምልክት የሆነው በዚህ ዘመን ትልቁ የእውነተኛ እምነት ተግዳሮት የመስቀሉን መከራና ሞቱን መቃወምና መካድ መሆኑን ያስተማረው ከእኛም ሆነ በዘመናት ሁሉ የመስቀሉን ክርስትና ከሚያምኑና ከሚኖሩበት ልዩና ዋነኛ ትምህርት ነው።

በየዘመናቱ ከክርስቶስ የመስቀል መከራና ሞት ጋር የሚጣረሱ ትምህርቶችና አባባሎች በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሰይጣን ሰዎችን ከዚያውም ክርስቲያን ነን ባዮችን በመጠቀም እያቀረበ እያሳተ የመስቀሉን ትክክለኛ ክርስትና ከማጥፋት የሚይቻለውን ሙከራ በማካሄድ ላይ ይገኛል። ከዚህም የተነሳ አያሌ ክርስቲያኖች ሕይወታቸውን ከጌታ መስቀል ይልቅ በዓለምና የሥጋ ሽክሞችን በመሸከም የክርስትና ሕይወታቸው እየተበላሸ ሌሎቹን እያበላሸ ከሕይወት ውጭ ሆነዋል።

ጌታ እንዳስተማርነው ሰው የሁለት ጌቶች ንብረት መሆን አይችልም የጌታ ወይም የሠይጣን *"ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም"* *(ማቴዎስ 6፡24)*

በሀገራችን የመንገል ስርጭት ታሪክ አቻ የሌለው በራሪ ጽሑፍ (ትራክት) ሕይወት ወይም ሞት የሚለው ብቸኛው የእምነት መለያ ጥሪ ነው።

በክርስትና የድል ሕይወት የሚጠፋብን በጌታ ጸጋ ደህንነት ያገኘንበት እምነት የሚሳሳበት የሚጎዳበት የሚኮሰሸበት ብቸኛው ምክንያት ይህ ሕይወትን ወይም ሞትን ከይቶ በእምነት ያለመኖር የተደበላለቀ የሚቃረኑ ሕይወትና እንደበትን መያዝ ነው።

ከዚህ መደበላለቅ በእምነት መክሳት መጠለፍ መባዘን መሳት ብቸኛው መንገድ አንድና አንድ ብቻ ነው፤ ክርስቶስ ወይም እኔነት። ይህንን የሙሴ ተተኪ ከባርነት ነፃ የወጣው የእስራኤል ሚሳበረሰብ ዛሬም በክርስቶስ አዲሱ እስራኤል ከተባለው የክርስቲያን ማህበረሰብ የተሰጠ ትንቢታዊ መሳኝ ምርጫ ነው። ሕይወት ወይም ሞት *"የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ"* *(ኢያሱ 24፡15)* የምትከተሉትን እምነት ቤተክርስቲያን ማሳበር ዛሬ ምረጡ ክርስቶስ ወይስ እኔነት?

የብዙ ክርስቲያኖች ችግር በክርስትና ሁለት ብቻ አማራጮች እንዳሉ ያለማወቅ ወይም እያወቁ የማደበላለቅና ከራስም ከሌላውም መርገምን ሙድቀትን ማስከተል ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክም ሰውም የሆነው ያስተማረን የራስ የእኔነት ፍላጐት ላይሆን የእግዚአብሔር ፍላጐት ቢያመንም እንድንመርጥ እንድንከተልና እንድንቀበል ነው። *"ብትፈቅድ ይህችን ፅዋ ከእኔ ሙሰድ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ"* *(ሉቃስ 22፡42፣ ዕብራውያን 10፡9)*

ጌታችን ጴጥሮስ እንደሚከደው አስቀድሞ የተረዳውን ተናግሯል። ጴጥሮስ በገረድ ፊት ክዶታል። ሆኖም ግን በቤተክርስቲያን ታሪክና በሐዋርያት ሥራ ላይ እንደተጻፈው ጴጥሮስ ራሱን በመካድ ክርስቶስን ሲመሰል ሞትን ሳይቀር የሚይፈራ ኃያል የመንጌል ሰባኪ ሆኖ በሞት ሲቀጣ እንደጌታዬ ሳይሆን ቁልቁል ስቀሉኝ በሚለት የከበረ የእምነት መሥዋዕትነትን ተቀዳጅቷል። (ሐዋርያት 4፡13)

ሐዋርያው ጴጥሮስ በገረድ ፊት ጌታን ከካደ በኋላ ጌታ ሲመለከተው ስቅቅ ብሎ ያለቀሰው እኔነቱ ከክርስቶስ እምነቱ ጋር የመጋጨቱ ጸጸትን መንፈስ ቅዱስ ስለሰጠው ነው። (ሉቃስ 22፡62)

እንደ ጴጥሮስ ከጌታ የገባነውን ቃል ኪዳን እኔነት ሲገዛን መንፈስ ቅዱስ በቃሉና በመገኖች ደርሶልን ልባችንን ሲነካው በንስኃ መመለስ ከእኛ ትምህርት ይሁንን እንደ አስቆሮቱ ይሁዳ በጸጸት እራስን ከሚጥፋት ጌታችን ይጠብቀን።

እኔነትን በተሞካ ሕይወት የክርስቶስን መስቀል ባስወገደ ክርስትና ትእቢትና አብሪት እየበዛ የጌታን ሥራ ወደሚገዳደር ልምምድ ሲብስም የጌታ ጠላት ከመሆን ጌታ ራሱ ይጠብቀን ዘንድ እንሚጸን።

በእኔነት ከመመካት የመጣው ኬላው ሐዋርያ ጳውሎስ እጅግ ከፍ ያለ የጌታን ምስጢሮች ሳይቀር የተረዳው እኔነቱን የጋረደበትን ቅርፊት ጌታ ስላስወገደለት ነበር:: (የሐዋርያት ሥራ 9) ጌታ የካከበት ሀመልምም እኔነቱን እንዲረዳ አደረገው (2 ቆሮ. 2)።

<u>የመስቀሉ ሥራ ከክብር እክሊል ሥራ ይቀድማል</u>

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃሉ እንደተጻፈ የመከኮት ክብሩ የተገለጸውና ካመኑት የታየው ከመስቀሉ ሥራ ከመታሰሩ ፣ ከመሰደቡ፣ ከመገረፉና ከመስቀሉ በኋላ ነው።

"የሚያልፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ ይሰድቡት ነበርና። በቴ መቅደስን የምታፈርስ በሦስት ቀንም የምትሠራው፣ ራስህን አድን የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንክ ከመስቀል ውረድ አሉት" (ማቴዎስ 27፥39፣ ኩቃስ 22፥35)

ሰይጣን የእግዚአብሔር አቅድ መሆኑን የሚቃመመው ብዙዎች እንዲድኑ ኪከናወን የተገባውን የመስቀሉን ቃል የጌታን ሀማማት ኪገልጹና ምስክርነት ኪያጡ አይችልም። ምን ያህል ሰይጣን እንደጌታ ትንቢት በመስቀሉ ሥራው ላይ መሰናክልና ጥፋት እንደሚያቅድ ከቅዱስ ቃሉ እንረዳለን።

ከዚህ የሰይጣን የመስቀሉ ሕይወት ማሰናከያ ተንኮሎች አንዱ ጌታን ፈትኖበት ያልተሳካለት ከአማኞች ሁሉ ትምህርት የሚዳን ሥራዎቹን የሚያጣጥሉና የሚያስክዱ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶችና ፕሮግራሞች ማቅረብ ናቸው።

ሰይጣን ከክርስቶስ የመስቀሉ ሥራ ጥላቻዎች እንዲበራከቱና በአማኞች ሕይወት የመስቀሉ መልዕክት እንዲጠፋ እንዲሳት የሚያደርግበት የዘመናችን አስከፊው ልምምድና ስብከት ታዋቂ በተባሉ ሰባኪዎችና ስም ብቻ በያዙ ቤተክርስቲያን ተብዬዎች ቀጥሏል።

ሆኖም ግን በክርስትና የተነሳ በአለማችን የተገኙት የስልጣኔና የሰው ልጆች እኩልነት መርህዎች ሁሉ የተገኙት የመስቀሉን መከራ በተካፈሉ ቅዱሳን አገልግሎቶች መሆኑን ተጨባጭ ታሪክ ይመሰክራል።

ሰይጣን ከጌታችን አገልግሎት ጅማሬ አንስቶ የመስቀሉን መከራ ከማስወገድ ብዙ ማባበሎችን ቢያደርግም ጌታችን የሰይጣንና የዚህ ዓለም ክብርን የዓለምን ሚታለል ሳይቀበል በመስቀሉ ሥራ ቀጥሎ ዓለምን የሚዳን ሥራውን ፈጽሟል። (ማቴዎስ 27፥40፣ ኩቃስ 4፥5፣ ዮሐንስ 12፥24)

ጌታችን በጸሙ ወራት ሰይጣን በሥልጣን ችሮታ በቃሉ ጭምር ከሚሣሣት ያደረገውን ጥረት በጴጥሮስም በኩል ስቅለቱ እንዳይካሄድ ያደረገው ጥረትና ማባበል ሁሉ ዘላለማዊ ክብር የሚያስገኘውን ከመስቀሉ መከራ በኋላ የሚገኘውን ክብር ከማስቀረት ነበር። ጌታችን ግን እግዚአብሔር እንድያ ልጁን በማዳን መካእከቱን ሳይቀር ኪልክ እንደሚችል ከገለፀ በኋላ የመስቀሉ ስቃይ ኪመጣ ካለው ድልና ዘላለማዊ ሕይወት መሠረት መሆኑን ይህም የትንቢት ፍጻሜ እንደሆነ አስተምሯል (ማቴዎስ 26፥53)

በአሮጌ አቁማዳ አዲስ ወይን ጠጅ እንደማይቀመጥ ጌታችን ያስተማረው ምሳሌ በአሮጌው አዳም ሕይወት የአዲሱ አዳም ክርስቶስ ጸጋና ፍቅር የዘላለም ሕይወት እንደማይገኝ አስረግጦ በማስተማሩ ነው (ኩቃስ 5፥36)

አሮጌውን አዳማዊ ባህርይና አእምሮ ወደ አዲሱ አዳም ክርስቶስ ሕይወትና አእምሮ ኪመልስ የቻለ ብቸኛው የእግዚአብሔር መንገድ የመስቀሉ የመከራ ሂደት ብቻ ነው (ገላትያ 2፥20፣ ገላትያ 6፥14)

ብዙ የመስቀሉ አገልጋዮች በከፍተኛ ትጋት የክርስቶስን ቃል ካቀረቡ በኋላ በዓለም በሚገኝ ደስታ ምቾት ዝናና ክብር ጥቅም ፍለጋ መስቀሉን ጥለው በአሳዛኝ ፍፃሜ ላይ የደረሱትን በቤተክርስቲያን ታሪክ እናገኛለን።

የመስቀሉ ላይ የክርስቶስ ስቃይና ሞትም ሆነ አስቀድሞ በዓለም የደረሰበት መገለል መመገዝ መሰደብ መገረፍ አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን የተገለጹ የክርስቶስ የመሲሁ የመስቀል መከራን የሚያረጋግጥ እኛም ተከታዮቹ ልንቀበለው የተገባ መሆኑ ተጽፎልናል (መዝሙረ ዳዊት 118፥27፣ ኢሳይያስ 53)

አማኞች ከክርስቶስ የሚለዩትና ከዓለምና ከሥጋ ምኞት ጋር የሚደራደሩት ከሰይጣን የጥፋት ኢላማ የሚሆኑት የመስቀሉን ሥራ ስለዱ ሲያሳንሱና ሲያሳስቱ መሆኑን ቅዱስ ቃሉም ታሪክም ይመሰክራሉ።

እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ያለው እቅድ መልካም በጎና ያማረ ቢሆንም ሰይጣን የተሰጠውን ኃይል ተጠቅሞ በሚነዛው ክፉ ትምህርት የተነሳ የተበላሸውን ፍጥረት ከማቅናትና የእግዚአብሔርን ፍጹም በረከት ከመቀበል ብቸኛው መንገድ የመስቀሉ ቃልና ሥራ ብቻ ነው። *"በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ (መስቀል) በኩል ድል መንሳት ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን"* *(1ኛ ቆሮንቶስ 15፡57)*

የመስቀሉ ትርጉም (በማየር)

"በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን" (ፊልጵስዮስ 2፡5)

የእምነት ጉዳይ ዝም ብሎ ምሁራዊ ትንታኔ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ከቃሉ የተነሳ ፍጹም መታመን ያለበት በፍሬ የሚታይ ሕይወት ነው።

ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ እስከመሞት ድረስ ትሁትና ታማኝ በአባቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ታገዥ ሆኗል። (ፊልጵስዮስ 2፡8) ክርስቶ ይህንን ራሱን እስከሞት ደረጃ መድረስ ያበቃው በመስቀሉ መከራና ሞቱ ስለሆነ የመስቀሉ ቃልና መልእክት ከዓለማዊያን ከተፈጥሯዊ ስጋዊ ሰው ባይመችም ባይገባውም ለእኛ ለምንድነው ግን ትልቅ የእግዚአብሔር መልእክትና የክርስትና መሠረታዊ መርህ ነው።

"የመስቀሉ ቃል ከሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና" (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡18)

በደረታች በእንገታችን በቤተክርስቲያናችን በቤታችን ላይ የምናስቀምጠውን መስቀል ትክክለኛ ትርጉም ተረድተን እንከተለው።

የሚል መንፈሳዊ መነቃቃት ንስኃና መመለስ ከሀገራዊና ዓለማቀፋዊ መነቃቃት መሠረት ነው

በዓለማችን ላይ ከአዲሱ አዳም ከጌታችንና መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጀምሮ የሰው ዘርን በሰይጣን ሚሳሳት የተነሳ ከጠፋበት ኪመልስ የሚችለውን የእግዚአብሔር ጉብኝት የሚያመጣው ሥራ የሚጀምረው በሚል እግዚአብሔርን ከመሚጸን በትህትና ከፈቃዱ ከመገዛት ይጀምራል። (ዮሐንስ 7፡37)

ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች በቅዱስ ጥምቀቱ የታተምን ይህ የሚል የመነቃቃት በትህትና ከእግዚአብሔር ቃልና ፈቃድ መታዘዝ ያስፈልገናል።

ከእግዚአብሔር ቤት አገልግሎትና ከየምሥራቹ የወንጌል አገልግሎት ሥራ ትልቁ ተፈላጊ ነገር አሮጌው አዳማዊ ማንነት በአዲሱ አዳም በክርስቶስ አእምሮ መሞላትን በመንፈሱ መታደስ ብቻ ነው (ሮሜ 12፡2፣ ኤፌሶን 1፡17)

በሰው ልጅ እንቅስቃሴ ከድርጊት በፊት ሚሰብና አእምሮን መጠቀም የፈጣሪ ልዩ ስጦታ በመሆኑ አእምሯችንን ከሚነኖሙም አገልግሎትና ሥራ በፊት በእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ እንመላው (መዝሙር 42፡1) (ፊልጵስዮስ 2፡5)

ጌታችን ከእኛ ያለው ፍቅር ልዩ ነው

ጌታችንና አምላካችን እግዚአብሔር እኛ አማኝ ልጆቹን ምን ያህል እንደሚወደን በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን በዝርዝርና በግልጽ ተጽፎልናል።

"የሠራህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ተቤኘርቼሃለሁና አትፍራ በስምህም ጠርቼሃለሁ፥ አንተ የእኔ ነህ ... በዓይኔ ፊት የከበርክና የተመሰገንህ ነህና እኔም ወድጀሃለሁ" (ኢሳይያስ 43፡1-3)

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" (ዮሐንስ 3፡16)

ከፍጥረት ሁሉ የሰው ዘር ከጌታ ልዩ ፍጥረቱ መሆኑን የምናውቀው እግዚአብሔር ሰውን ብቻ በራሱ አምሳል መፍጠሩን በገለጸበት በቅዱስ ቃሉ ነው (ዘፍጥረት 1፡27)

እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ከመፍጠሩ በላይ ሰው ከእርሱ ጋር ወዳጅ እንዲሆን የሚፈልግ አምላክ ነው። ይህም የእግዚአብሔር ከሰው ዘር ያለው ልዩ ፍቅርና ጥበቃውን ሰው በሆነው ልጁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾዋል። (ዮሐንስ 17፡3)

እግዚአብሔር ከሰው ጋር ያለው ግንኙነት ባማረ እንዲሆን መጀመሪያ በሰው ላይ ካፈሰሰው መንፈሱ በላይ ሕጉን በመቅረጽ ከሕዝቡ እንዲደርስ አድርጎዋል ከትንሹ እስከ ትልቁ ድረስ ሰው ሁሉ እግዚአብሔርን ያውቅ ዘንድ አዋጁን መመሪያውን ሰጥቷል (እብራውያን 8፡10)

የእግዚአብሔር ፍቅር ከፍጥረቱ ከሰው እጅ የበዛ መሆኑን በእግዚአብሔር በራሱ ቃል ተጽፎልናል (ሚርቆስ 12፥30፣ ሮሜ 5፥5)

እግዚአብሔር በሚያስፈሩ ሁኔታዎች ሳይቀር ከሕዝቡ ጋር እንደሚገኝ በታመነ ቃሉ የሰጠው ቃል ኪዳን ዛሬም የሚሰራና ልንጠብቀው የተገባ ነው። "እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ አበረታሃለሁ አረዳሀሃለሁ በጽድቁም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ" (ኢሳይያስ 41፥10)

"እግዙአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው" (መዝሙር 34፥17)

"መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው" (ዘዳግም 33፥27)

"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው የሚያሳጣኝ የለም" (መዝሙር ዳዊት 23)

በመጨረሻም ጌታ አምላክ ሕይወቱን ለተከታዮቹ እስከ መስጠት መልካም አረኝነቱን ገልጾልናል። "መልካም አረኛ እኔ ነኝ መልካም አረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል"

ክርስቶስ የእኛ ሕይወት ነው

ክርስቶስና ክርስቲያን አንድ ናቸው። በመጀመሪያ በክርስቶስ ኢየሱስ ያመኑትን ከሚጥሉት ከመለየት የጠሩበት መጠሪያ ክርስቲያን የሚለው ነበር (ሐዋርያት 11፥19)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱ እንዳስተማረው ተከታዮቹ ክርስቲያኖቹ በእርሱ ኪኖሩ እንደሚገባ ያለ እርሱ ምንም ሚድረግና ሚፍሩት እንደሚይችሉ በቅዱስ ቃሉ አስተምሮናል።

"እኔ የወይን ግንድ ነኝ አናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል" (ዮሐንስ 15፥5)

ይህን የጌታን ቃል እንዳለ መቀበልና በሕይወታች ይገለጽ ዘንድ መትጋት ይኖርብናል። በቀራንዮ መስቀል እይታ ይህንን መልዕክት ስንረዳ ጌታን የተሰቀለበት መስቀልና የተቀበረበት መቃብር በመስቀሉ ጌታ ኃይል መመገዱን እንረዳለን።

የብዙ ጎይሚኖቶች መሥራቾች አፅም በአርኪዎሎጂ ሲገኝ የአንዳንዶቹንም የይገለኛል ጥያቄ ሲያመላግብ የእኛ ጌታ ግን ሞትን ያሸነፈው አስከሬኑ አፅሙ ፈጽሞ አልተገኘም።

የእኛም የመጨረሻ እድል ፈንታ አንደ ክርስቶስ በትንሣኤ ደግሞ ሕያው መሆንና ከሞት ተነስቶ በተከታዮቹ መካከል ተገኝቶ ሰላም ለእናንተ ይሁን እንዳለው የጌታ ሰላምታ መለዋወጥ ይሆናል ሃሌሉያ!

"ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ፥ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥ በጸጋ ድናችኋልና፥ በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ፣ ከእርሱ ጋር አስነሳን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን" (ኤፌሶን 2፥4፥6)

ድል ነሺነት የክርስትና ባህርይ ነው ሆኖም ግን ይህ ድልነሺነት የተገኘውና የሚገኘውም በመስቀል መከራ በተቀበለው ኢየሱ ክርስቶስ የመስቀሉ ሥራ ብቻ ሲሆን እኛም ድል ነሽ የሆነውም በመስቀሉ ሥራ ብቻ መሆኑ ገብቶን ልንኖርበት ከመስቀሉ ከሚጣላ የብልጽግና ኑፋቄ ልንጠበቅ ያስፈልገናል። ሕይወታችን በመስቀሉ ሥራ በክርስቶስ ተጠቅልሎ ዘላለም ይኖራል (ቆላስያስ 3፥3)።

የክርስቶስ ዙፋንና የአሚኖች የየእለቱ ኑሮ

ወደጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር ዙፋ በመንፈስ ቀዱስ አነሳሽነትና ኃይል የምንደርሰው አስቀድሞ በክርስቶስ በተጠናቀቀው የመስቀል መከራና ሞቱ የተነሳ ነው።

ከዚህ ውጭ ክርስቲያኖች በራሳቸው ልምምድ ወይም በቤተ እምነቶቻቸው ሥራ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ይቀርባሉ የሚል ድምዳሜ የሳተና ከቅዱስ ቃሉ የሚጣረስ ይሆናል። *"በበጎ ፈቃዱ እንደመደዱ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለአርሱ (እግዚአብሔር) ልጆች ልንሆን አስቀድሞ መለነን"* (ኤፌሶን 1፥5)

"በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን" (2 ጴጥሮስ 1፥2)

ክርስቲያኖች ወደ ክርስቶስ ዙፋን የሚደርሱት በእነሱ ብቃት ሳይሆን ብቃትን ሁሉ የፈጸመውን ክርስቶስን በማመን በጸጋውና በምሕረቱ ብቻ ነው (ኤፌሶን 2፥8)።

"በእንዱም በደል ሞት በእንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን በጸጋን ብዛትና የጸድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በእንዱ

በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ" (ሮሜ 5፥17)

የክርስቶስ መራመድ እንደ ንጉስ በሙሉ ሥልጣንና በሙሉ ክብር ሲሆን የእኛ መራመድ ግን በእርሱ ተደግፈን እንደ ንጉስ ልጅች ልኡካን መራመድ ይሆናል (2ኛ ቆሮንቶስ 5፥7፣ ራእይ 1፥7)

በምድር ሕይወታችን የሚያጋጥሙን ተግዳሮቶች ሚድረግ የምንፈልገውን ያለሚድረጋችን ሚድረግ የሚንፈልጋቸውን ሚድረጋችን ያስከትሉብን ምስቅልቅል ኑሮና ጭንቀት ሁሉ ተወግዶ ሸክማችን ተራግፎ ድል በድል የምንሆነው ይህንን በሚመንና በመቀበል በክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ድል ነሽነናችንን ስንረዳ ነው (ሮሜ 7፥25)

ይህ በክርስቶስ በጎ ነገሮች መፈጸም መቻላችን አስቀድሞ በእርሱ የታወቀና የታዘዘ ስለሆነ ያለ እርሱ ምንም ሚድረግ እንደሚንችል ተረድተን የእርሱን እድራጊ አስደራጊነት አምነን እንደፈቃዱ እንደሀሳቡ ሁሉን እንድናደርግ እንሚጸነው እታመንበት "ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም" ዮሐንስ 15፥5)

መጀመሪያ በጌታ ሥር እንቀመጥና ሰምተነው እንራመድ

ክርስቲያን ከሁሉ በፊት አስቀድሞ የእግዚአብሔርን ፈቃድና አቅጣጫ ከእየለቱ ኑሮው በቅዱስ ቃሉና መንፈስ ምሪት መጠየቅና መከተል ይኖርበታል።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጀመሪያ ሚወቅ በእርሱ መታመን በራሳችን ሚስተዋል ያለመደገፍ የተሳካ ክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲኖረን ይረዳናል። *"በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን በራስህም ማስተዋል አትደገፍ" (ምሳሌ 3፥5)*

"አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግስት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል" (ማቴዎስ 6፥33) የእግዚአብሔርን ፈቃድና ሀሳብ የሚያስጀምረንም ሆነ የሚያስፈጽመን ከአሚኛች ሁሉ ቃል የተገባልን ጌታ መንፈስ ቅዱስ ነውና ሁልጊዜ በመንፈስ ቅዱስ መከሚመድ በጸሎትና በቃሉ ትጋት እንጋብዘው። (ዮሐንስ 16፥7)

አሮጌ ሰዋችን (እኛነታችን) ይከወጥ ዘንድ አዲሱን ሰው ክርስቶስ ሁልጊዜ መሚጸን በጥሞናችን መጋበዝና መምሰል ያስፈልገናል። (1 ቆሮንቶስ 11፥1፣ 2 ቆሮንቶስ 5፥17፣ ኤፌሶን 5፥2)

በክርስትና መራመድ የሚቻከውና እርምጃ የሚታወቀው እኛ ያለንበትን ሥፍራ በሚወቅ ጌታ ያለበትን በመረዳት ይሆናል። ጌታ ክርስቶስ በአባቱ ቀኝ ያለ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው አስከዓለም ፍጻሜ ከእኛ ጋር እንደሚኖር ቃል የገባልንና በክብር ኪመስደን የሚመጣ ጌታ ነው።

የእኛ ስፍራ ደግሞ ኑሯችን በምድር ቢሆንም በክርስቶስ የመስቀሉ ሥራ በሰማያዊ የክብር ሥፍራ ያስቀመጠን በዚህ ምድር ግን መጻተኛች የሆንን የእግዚአብሔር ልጅች ነን (ኤፌሶን 2፥6፣ 1 ጴጥሮስ 2፥9)

እኛ አሚኛች ከክርስቶስ ጋር አብረን እንደተሰቀልን በእኛም ኪኖር የሚገባው የእኛ አሮጌ አዳም ሳይሆን አዲሱ ሞትን ያሸነፈው ዘላለማዊው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን አምነን በእግዚአብሔር ምህረት እንራመድ ኬሎቹም ይህን አግኝተው ከዘላለም እንዲራመዱ ወደፍቅሩ የብርሃን መንግስት እንዲገቡ ከጨለማ እንዲወጡ እንጸልይ እንመስክር (ገላትያ 2፥29፣ 1 ጴጥሮስ 2፥9)

በክርስቶስ እንነሳ የተነሳውን ጌታ ኃይልም እንልበስ

(በቻርለስ ስፐርጂንና በአንድሬው መሉ)

በጥልቅ የክርስቶስ ከመሙታን ትንሳኤ ምስጢር ክርስቶስ ከመሞቱ በፊት ምን ሠራ? ወደ ጨለማው ዓለም መጥቶ ሚንም ኪያሸንፈው የሚይችለውን ሞትን አሸነፈ ሕይወት አልባ ከሆነው የሰው ልጅች ኃይሚኖት ሕይወትን ሰጠ። በክርስቶስ ሞት እደምንመለከው ሁሉ በእርሱ በሚመንም በትንሳኤው እንመለከዋለን። ከግብፅ ባርነት እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደጠራ ከዓለም ከሰይጣንና ከሥጋ ባርነት በአዲስ ኪዳን ጌታ ሕዝቡን ይጠራል ያመጣል (1 ጴጥሮስ 2፥9)

ቤተክርስቲያን በጌታ እግር ሥር ዝግ ብላ በንስኃ አስካልተመለሰች ድረስ ምእመናን የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያውቁ ሆነው በኃጢያት ላይ ኃጢያት ጨምረው በከፋ ልምምድ ተይዘው ይኖራሉ።

ከዚህ ከፋ ልምምድ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚወጣው የሚነሳው ከዓለም በመሞት ከክርስቶስ ጋር በመነሳት ነው።

ከሞት የተነሳው ክርስቶስ ካመኑት ልጆቹ በትንሳኤው ኃይል ይሞካቸዋል። በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልተው የሚያሳድዷቸው ነገስታትን ባለስልጣናትን ክፋ የጎደሚኖት መሪዎችን ሳይፈሩ ትንሳኤውን ያውጁ ነበር።

ክርስቲያኖች ይህን ሁሉ ታምራቶች የሚፈጽሙበት በሰው ጥበብና አእምሮ ሳይሆን ተስፋ በተገባላቸው በእነርሱ ላይ በሚፈሰሰውና የሚያንቀሳቅሳቸው ጌታ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው። *“ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ” (ማቴዎስ 28፥18)*

በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር ከአማኞች የሚሰጠው ኃይል እጅግ መለኮታዊ የሆነ በዓለም ላይ የሚይታይ ልዩ አደራረግ ያለው ሺዎችን ከክፋ የአለም መንገድ ከሰይጣን ወጥመድና ከሥጋ እስራት ነጻ የሚያወጣ የጌታ መንፈስ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስሙ ከሚያምኑትና ከተቀበሉት የሚሰጠው ሥልጣንና ጸጋ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኘውን ኃይል ነው። የምድራዊ ልዩ ልዩ አነቃቂ ትምህርቶች ምድራዊ ሁኔም የሚጐዱኩ ሲሆን ጌታ የሚሰጠው ግን ዘላለማዊ ነው።

<u>የመታዘዝ ፈተናዎች</u>

እግዚአብሔር በየጊዜው የሚፈተኑ ልጆች አሉት። ከእነዚህ ከፊሎቹ ፈተናውን በድናት በብቃት የሚወጡ እንዳሉ ሁሉ ኔሎቹ ደግሞ በጎውን ፈተና የሚያልፉ ዘወትር በኃጢያት ፈተናዎች ሕይወታቸው እንዲሰጥ ምክንያት የሚሆኑ ናቸው።

ከእግዚአብሔር ምንያህል እንደታዘዝን የበላናቸው ምግቦችን ጭምር የሚያውቁ ሰውር ምስክሮች አኩ። ከዚህ በተቃራኒው በእውነት ከእግዚአብሔር መንግሥትና ከፍሬዎቹ ቀን ከሌሊት የሚያግሙና በመጠነኛ መተላለፋቸው ከአሰር ወደ አሰር የሚዳርጋቸው ዛሬም ድረስ ይኖራሉ።

ጌታ እግዚአብሔር ከብዙይ ዘመን ጀምሮ መጽሐፍትን የሚያስተምር ሲሆን በድርጊቱ የተለዩትን ኔሎች ሰዎች ወደ ንስኃ እንዲመጡ ከጌታ ሥራ ታምነው እንዲሰሚሩ ቅዱስ ቃኩ በግልጽና በዝርዝር ያስተምረናል።

በዚህም እግዚአብሔር የአባትነት ሥልጣኑን በተመቸው መንገድና ጊዜ እንዲገልጽ ፈቃዱን እንዲያሳይ ልጆቹ በፍቅርና በምህረት ጌታ እግዚአብሔርን እንዲከተኩ ያሳል።

ከእግዚአብሔር ቤተሰቦች ጌታ ያደረገላቸውን በማክበርና በማወቅ ራሳቸውን ዝቅ ከሚያደርጉትም የተለዩ ሰዎች የሆኑት እንደጌታ በትህትና ፈተናውን በሚከፋቸው በእግዚአብሔር መፈተን በአምንታዊ መልኩ የምንቀበለው ነው። እግዚአብሔር በበጎ ይፈተናል። የሁለቱን ፈተናዎች ልዩነት በእምነት አባታችን አብርሃም መፈተን የታየ ሲሆን ሰይጣን ደግሞ አናታችን ሔዋንን በማሳሳት ያመጣው የጥፋት መንገድ ዛሬም ድረስ ክፉውን ሞት የሚያመጣብንን እንደ መልካም ነገር እያሳየ ይፈትናል። (ዘፍጥረት 3፥1፣ ዘፍጥረት 22፣ ማቴዎስ 4፥9)

እግዚአብሔር በበጎ የሚፈትናቸው ሁኩ ከነበራቸው ሀብት በረከት እውቀት ሁኩ በላይ እንዲያገኙ ጌታ በፈተናው ብቃትን ይሰጣቸዋል (ኢዮብ 23፥10)።

“ፍጹማንና ሙኩ ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም፤” (ያዕቆብ 1፥4)

“በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለምስጋናና ለክብር ለውዳሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል” (1 ጴጥሮስ 1፥6)

በሕይወታች ከእግዚአብሔር የሚገጥመንን ሁኩ በመታገስ በእርሱ በማክፍ የእግዚብሔርን ክብርና ዘላለማዊ ሕይወት እንካፈላለን።

<u>የግል የጥሞና የመታደስ አስፈላጊነት</u>

በግል ሕይወታችን የሚያጋጥመን ሽክም ሕመም ፈተና ችግር ሁኩ ወደ እግዚአብሔር የሚያመለክተን ከግል ንስኃና የመታደስ በጥሞና ሕይወት የሚያበቃን ነው።

በእስራኤላውያን በብዙይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ ምላሌነት በሚታወቁት ዘንድ የደረሰባቸው ችግር ባርነት ስደት ግዞት ሁኩ በእግዚአብሔር ነብያትና ካህናት በኩል የጌታ መልዕክት የሚመጣላቸው ከበረከትና ከችግሮቻቸው ከባርነት ከግዞት ከረሀብ የሚወጡበትን ሲያመቻችላቸው ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ በንስኃ ጥሪ በመቀስቀስና በማነቃቃት ነበር።

“አሁንስ ይላል እግዚአብሔር በፍጹም ልባችሁ በጾምም በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ” (ኢዩኤል 2፥12)

“እላችኋለሁ አይደለም ነገር ግን ንስኃ ብትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ” (ኩቃስ 13፥3)

“የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ከአናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ

ኃጢያታችሁም ይደመሰስ ዘንድ ንስኑ ግዑ ተመለሱም" (ሐዋርያት 3፥19)

ወደጌታ ከመመለስ በሙሰጣችን ያለ ኃጢያትን በመናዘዝ ቅዱስ መንፈሱን እንሞላ (ኤፌሶን 1፥17)

በዓለም ኑሯችን ላለን የሚያጋጥመን ፈተና ዓለማዊነት የሰይጣን ሥራና የሥጋችን ፈተና ልክ በበረሃ በሙሃ ጥም እንደምትቃትት እንስሳ በመሆኑ የሚያረሰርሰውን የሕይወት ጥማችንን የሚሞላልንን ጌታን እንድናገኝ ወደ ሕይወት ምንጭ ጌታ እንገስግስ። "ዋላ ሙኃ እደምትናፍቅ ነፍሴ አንተን ፈለገች" (መዝሙረ ዳዊት 42፥1)

ማንኛውም የክርስቶስ ተከታይ በየእለቱ ሕይወቱ መጀመሪያ በእግዚአብሔር ቃልና በቅዱስ መንፈሱ ተሞልቶ መንቀሳቀስ ይገባዋል፤ ይገባታል፤ ይገባናል።

ከብዙ መንፈሳዊ ሙድቀት ከግለሰብ ከቤተሰብ ከማህበረሰብና ከሀገር መፍረስ ምክንያት የሆኑ ሰዎች ሕይወታቸው በክፉ ሰይጣን የተሞላ ሲሆኑ ክርስቲያኑም ይህን የዓለም ክፋት በእግዚአብሔር ቃል በጸሎት በጾም ካልመከተ ይልቅ የከፋው አጋንንት ገብቶበት የበለጠ ጥፋት የሚደርስ ይሆናል። (ማቴዎስ 12፥45)

በሌላው መልኩ ጌታን ያሳዘኑ የካዱ በብርቱ ንስኃ ሲመለሱ የጌታ መንፈስ በእጥፍ እየገዘቸው ከብዙዎች መዳን ምክንያት ይሆናሉ። (ሐዋርያት ሥራ 2፥4)

<u>ከእግዚአብሔር ክብር መገለጥ አማኞች ሥርዓት ያስፈልጋቸዋል</u>

በእግዚአብሔር ቃል በሥርዓት መኖር የእግዚአብሔር ፍርሃት በአማኞች ሕይወት መገለጥ የመንፈሳዊ ጉብኝት ቀዳማ ተፈላጊ ሁኔታ ነው። ክርስቲያኖች በዚህ ሁኔታ ራሳቸውን ሳይገዙ በልበ ደንዳናነት በትእቢት በክፉ ንግግር ይባስ ብሎም በኃጢያት እየተመላለሱ ሥርአት ባለ ሕይወት የጌታ ክብርና ኃይል በፍጹም አይመጣም። *"በሰማ የተጠሩት ሕዝበ ሰሙነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ ፊቴንም ቢፈልጉ ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ ኃጢያታቸውንም ይቅር እላለሁ ምድራቸውንም አፈውሳለሁ" (2 ዜና መዋእል 7፥14)*

ሥጋችን ዘወትር በእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ላይ የሚነሳ ክፉ ጠላት ሲሆን መፍትሄውም በጌታ ቃልና በጸም በጸሎት ራስን ማስገዛት ነው። (ገላትያ 5፥17፣ 1 ቆሮንቶስ 9፥25) *"ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልኩ እንዳልሆን ሥጋዬን እየገመደኩ አስገዛዋለሁ"*

ሥጋችን በቃሉ በጸምና በጸሎት ካልተገዛ ከአለም የሚደርገን ይሆናል። "አገልግሎታችንም እንዳይነቀፍ በአንዳች ነገ ማሰናከያ ከቶ አንሰጥም በመጦም በንጽሕና በእውቀት በትእግስት በቸርነት በመንፈስ ቅዱስ ግብዝነት በሌለው ፍቅር በእውነት ቃል" (2 ቆሮንቶስ 6፥3-6)

የክርስቲያኖች ውጊያና ፍልሚያ በአካል ሳይሆን መንፈሳዊ በመሆኑ ከመንፈሳዊ ውጊያ እንቅፋት የሆኑ መሻቶቻችን የሥጋ አምሮትና አስተሳሰባችን ሁሉ በቅዱስ ቃሉ በጸምና በጸሎት መቃናት ይኖርባቸዋል ያንጊዜም ድሉ በክርስቶስ የእኛ ይሆናል ከአሸናፊዎች ሁሉ እንበልጣለን የሚለው የተሰፋ ቃል የእኛ ይሆናል (ኤፌሶን 6፥12፣ ሮሜ 8፥37)

የክርስትና ጉዟችን ሰማያዊ ሽልማትና ክብር እንዳለው ሁሉ ይህን ጉዞ ትተን ወደአለም ከተመለስን ደግሞ ቅጣታችን በእግዚአብሔር ቃል የተረጋገጠ ስለሆነ በጭምነትነት ከዓለም ከሰይጣንና ከሥጋ ሥራ ተለይተን ተጠብቀን የሕይወት ጉዟችን የእምነት ሩጫችንን እንፈፅም (2 ጢሞቲዎስ 2፥4-5)

<u>ማሳሰቢያና የፀሎት ርእስ ለኢትዮጵያ ቤተእምነቶች</u>

ሀገራችን ኢትዮጵያ በቅዱሳት መጽሐፍት ቀድመውና በብዛት ከተጠቀሱት ሀገራት አንዷ ናት። በታሪክና በሥነ ቅርስም እንዲሁ ቀዳማ ሆነ ሳለ የሚፈራረቅባት ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋና መከራ እጅግ የሚያሳዝን የሚያሳፍርም ነው።

የሚያሳዝነው የተፈጥሮ አደጋ ድርቅና የመሳሰሉት ሲሆኑ የሚያሳፍረው ደግሞ የከበረ ታሪክ ያካቸው ሕዝቦቿን በዓለም ዙሪያ ምሁራን በውጭ ሀገራት በብቃት የሚያገለግሉባት ኢትዮጵያ ያኳትን ቅርሶችና የተፈጥሮ ሥጦታዎች በተከፋ የሰው ኃይል በመልካም አስተዳደር ለህዝቦችዋ በክፉ ፖለቲከኞች ሴራ ከጥንት ከነገስታቱ እስከ ዛሬ ድረስ ባሉትና ወቅቱ የዘር ፖለቲከኞች አንዱ ከሌላው እጅግ የተደባለቀ ተመሳሳይ የሆኑ ሕዝቦች የሚያባራ መተላለቅ ተጠምደው ከክፋው ድህነትና ረሀብ ላይ ተጨማሪ ረሀብና ድህነት ማስከተላቸው ሀገሪቱን ማቆርቆዛቸው ነው።

ይህን የሀገራችንን የተዛባ የመሬትና የሀብት ክፍፍል ከማስተካከል በተደረጉ ከሙሶች አያሌ መጣቶች

ምሁራን ባለፉት መንግስታት ከእስር ከግድያ ከስደት የተደረጉ ሲሆን ዛሬም ተባብሶበት ይልቁንስ በአስቀያሚ መልኩ በዘር ልዩነት ጥላቸው በፍቅር ቤት በተባሉት ቤተ እምነቶች ሳይቀር ተስፋፍቶ መንገሱ ነው።

ይህንን ግፍ በደል በሚየት ቤተክርስቲያን እንደነብይ መምከር መገሰጽ ሚውገዝ ሲገባት የከፉ ገዢዎች ተባባሪ ምንደኛ መሆኗ እጅግ ያሳዝናል (ትንቢተ ኤርሚያስ 7፥1-12)

የሰዎች ባርነትና ቅኝ ተገዥነት ይቁም ዘንድ ሕይወታቸውን ጭምር የሰጡ የሰው መብት ተሟጋቾች። ፓስተር ሚርቲን ኪተርኪንግና የመሳሰሉት የሀገራችንም መንፈሳዊ ጥቂት መሪዎች ሲኖሩ ኬሎቹ ገዥዎችን ሺ ዓመት ያንግስ እያሉ በዝምታ መሞጣቸው ጭራሽ መተባበራቸው እንዲቁም የተገፋው፣ የሚሰደደው፣ የሚፈናቀለው ሕዝባችን ድምጽ ይሆኑ ዘንድ እናሳስባለን፣ እንመክራለን።

ባለፉት የኢትዮጵያ መንግስታት ዘመናት መሬት ለገባሩ ለአራሹ እንዲሰጥ በነበረው የንጉሱ ፓርላማ ሳይቀር የመሬት ይዞታ ሥሪት ሚሻሻያ የሚል ያቀረበችው መንፈሳዊት መኳንኢየሱስ የቀድሞ መሪዎችን ትውልድም ሆነ ፈጣሪ በታሪክ ሲዘግባቸው ይኖራል (ኤፌሶን 3፥21)

በመቀጠልም የሀገራችን የዘር ፖለቲካ ሕዝባችንን እንዳይጨርስ በግዮን ሆቴል በተደረገው ሃገራዊ የእርቅና ሰላም ጉባኤ መንፈሳዊት መኳን ኢየሱስ በይፋ መሳተፍም እጅግ የተከበረ የመንፈስ ኃላፊነት ተግባር ሚደታና መብት ነው።

ዛሬም መንፈሳዊትና ኬሎቹ የእምነት ቤተሰቦች የሀገራችን ሰቆቃ ግፍ ይቁም ዘንድ ለህዝባቸው ኪጮኑ ኪሞግቱ ይገባል። ይህንን ኃላፊነት የሚይመጣ ቤተእምነት በታሪክ ሲመቀስ ይኖራል። ቤተክርስቲያን ሆይ ድምጽሽን አሰሚ!

በተለይ በዚህ ወቅት የመንፈስ አሚኖች በኢትዮጵያ ማኅህበረሰቦች እያገኙ የመጣውን በጎ ተቀባይነት ተሰሚነት የሚያጎድፍ የሳተው የብልጽግና ተብዬ አስተምህሮን የመንፈሳዊት መሪዎች ኪርቁት ኪያመዝኑት ሲገባ ከእነዚህ ሀሳዊ አጭበርባሪዎች ጋር እንዲጣመሩ የሚተጉ ድርጅቶች ጋር መተባበር እጅግ የሚያሳፍር ተግባር ነው።

በአርዮስ የስህተት ትምህርት የተነሳ ንጉሱ ቆስንጠንጢኖስ የጠራው የኒቅያ ጉባኤ ኑፋቄን በሚጋለጥ በመገሰጽ አልመለስ ያለውን አርዮስን አወገዘ እጅግ ከቅዱሳን ኅብረት ትብብር ወዳጅነት ያካደረገው ትምህርት ይሁንን በመስቀሉ ቃል መደራደር ይብቃን የጤናማ መሠረተ እምነት ያካቸው አብያተክርስቲያናትም አዲስ ከሚያቋቁመት በቅዱስ ቃሉ ህፀፅ አስከሌለ ድረስ በሐዋርያቱ ፈለግ በፍቅር ኪቀበሏቸው ኪደግፉቸው ይገባል (የሐዋርያት ሥራ 15)

ጌታ እግዚአብሔር የኢትዮጵያን ጉስቁልና ያስወገድልን የተስፋ ቃሉን ይፈጽምልን (መዝሙር 68፥31)

<u>የምጽአቱ የምሥራች ተባባሪ አገልግሎቶችና ትብብር ጥሪ</u>

የምጽአቱ የምሥራች በሚል መጠሪያ በኢትዮጵያ ዘመን በ1983 ዓ.ም መጋቢት መር ትርጉሙ የተጀመረው Herald of His Coming የተባለው የመንፈስ መነቃቃት ዓለም አቀፍ አገልግሎት ነው።

የዚህን አለምአቀፍ አገልግሎት ጥሪ ተቀብሎ የትርጉሙን አገልግሎት በነፃ በሚስተባበር በተለያዩ መንፈሳዊ ርእሶችን ተርጓሚው አደፍርስ (ኤዲ) ሀብቱ መኳሻ ከባለቤቱ ፋንታዬ ግርማ ጋር እስከ ዛሬ ድረስ እንዲቀጥል ለረዳው ጌታ ኢየሱስ ክብርም ምስጋናም ይሁን።

1. የምጽአቱ የምስራች መንፈስ ሚድረስ አገልግሎት

ይህን የትርጉም ሥራ የሚያስተባብር የሚያትምልን በአሜርካን አገር ያለው Gospel Revivals አገልግሎት የአሜሪካን የጸሎት ኅብረት ተባባሪ ሲሆን የኢትዮጵያ ሸክም ያላቸው ናቸው።

ከዚህ አገልግሎት ከደቡብ አላባ ቁኪቶ እስከ ሰሜን እንዳስላሴ ትግራይ ኤርትራ እስከ ምዕራብ ኢትዮጵያ ጋምቤላ ድረስ ሥርጭቱ ይካሄዳል።

2. ታላቁ ተልእኮ አገልግሎት

በቅርቡም አሳታሚዎቹ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን በነፃ የሚልኩልን ሲሆን የእንግዚዝኛ እትም ተጠቃሚዎች በሺዎች በኢትዮጵያ ይገኛሉ። የታላቁ ተልእኮ አገልጋዮች ስልጠና ሰጥተውናል። በቅርቡም በኢትዮጵያ በይፋ ፕሮግራም ይጀመራል። ይህን አገልግሎት በጸሎትና በሚቻለው ሁሉ በመደገፍ የጌታን ሥራ ማገዝ ነውና አንባቢዎች ሁሉ በዚህ እንዲሳተፉ አጠይቃለሁ።

3. የምህረቱ አምባና ፍቅር ምህረት አለምአቀፍ አገልግሎት

በቅርቡ ያዋቀርነው የምህረት አገልግሎት ከፍቅር ምህረት ዓለም አቀፍ ጋር በመተባበር በክፉ በአታላይ ደላሎች

በሐሰት ወደውጭ ሀገር መገኖቻችን እየሄዱ በመከራ የሚዳረጉትን ከመመከስ በመተጋት ካይ እንገኛለን።

በዚህ የመመከስ ሥራ በቅርብ ጊዜ 500 በላይ ኢትዮጵያዊያን ከክፋት ጉዞ ተቆጥበው በሀገራችን በሔላ ጤናማ ሥራ ተሰማርተዋል።

ስለዚህ እነዚህን ተባባሪ አገልግሎቶች በመተባበር መገኖቻችንን የመደገፍ ሥራ እንድትሳተፉ አድራሻቸውን እንገልጻለን።

በምጽአቱ የምሥራች ተጠሪ አልማዝ አሳየ

0912120402/0913377328

የምሀረት አምላ ተጠሪ አናፍ አመንሲሳ

<u>የምጽአቱ የምሥራች ምስክርነቶች</u>

ከእንግሊዝ

ሁሉን ቻይ አምላክ የምጽአቱ የምሥራችን ስለሰጠን ስሙ የተመሰገነ ይሁን። ጋዜጣችሁን ከጎረቤቶቼ ጭምር በማካፈል እየተባረኩበት ነውና ሳታቋርጡ ላኩልኝ።

ከካናዳ

እድሜዬ 81 ደርሷል በልጅነቴ እናቴ የሰጠችኝ ይህን ጋዜጣችሁን እድሜዬን በሙሉ እየተባረኩበት ነው ጌታ አምላክ ይባርካችሁ።

ከናሚቢያ

ባለፈው ዓመት የመጋቢትና የሚያዚያ እትማችሁ ስለ ክርስቶስ መሥቀል ያስተማራችሁበት የልቤን አይን ከፍቶልኛል። ምንም ነገር የእኔ የምለው የሌለኝ በክርስቶስ የመሰቀል ሥራ የተገዛሁ የእግዚአብሔር እቃ መሆኔን እመሰክራለሁ።

ከአውስትራሊያ

በዘመናችን ሁሉ የጠቀመኝ የሚያነቃቁኝን የምጽአቱ የምሥራችን ጌታ ስለሰጠኝ እጅግ አመሰግነዋለሁ ተባረኩልኝ።

ከቦንጋ (ኢትዮጵያ)

የምጽአቱ የምሥራች የክርስትና ትርጉምን በሚገባ የገለፀልኝ በአዲስ ልምምድ መኖርን አስተምሮኛል። ቤተክርስቲያን ከዘመኑ ክፋት ትጠበቅ ዘንድም ፀልዩልን።

<u>የመዳን መንገዶች</u>

ማንኛውም ሰው ከየት መጣሁ ወደት እሄዳለሁ የሚለውን መልስ ከሚሰጠት መጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስን ያንብብ።

የበለጠ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ከሕይወቱ ከማወቅ የወንጌሉ ክፍሉን ከዮሐንስ ወንጌል ጀምሮ ያጥና ቀጥሎም

1. በቅርብ ወደሚገኝ ክርስቶስ ወደሚሰበክበት ማህበር ይዝለቅ። በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ እምነት ይቀጥል (ማቴዎስ 28፥19)
2. በዚያ ሀብረት ካሉት ወገኖች ጋር መጽሐፍ ቅዱስና በጸሎት ማህበር ይሳተፍ (ሐዋርያት 2፥44)
3. የሰማው ቃል ከሔሎች በማካፈል ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ የሚፈልገውን ጌታን ትእዛዝ ይፈጽም (ሮሜ 10፥9)

<u>ማሳሰቢያ ከአማርኛ ተከታታዮች</u>

የምጽአቱ የምሥራች የወንጌል አገልግሎት በኢትዮጵያና በዓለም ዙሪያ አማርኛን ከሚያነብቡ ወገኖች በነጻ የሚሰራጭ አገልግሎት ነው።

በዚህ አገልግሎት ከሰዎች የምሥራች ወንጌል ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ እየተሰራጨ ብዙዎች በጌታ በርትተዋል አዲሶችም አምነዋል።

አገልግሎት በአንባቢያን መዋጮ የሚካሄድ በመሆኑ የምትችሉትን በፖስታ ቤት በመላክ ተባበሩን በጸሎታችሁም አስቡን።

የምጽአቱ የምሥራች አገልግሎት ተጠሪ በኢትዮጵያ አልማዝ አሳየ 0912120402

የፖ.ሳ.ቁ 8689 አዲስ አበባ

አደፍርስ (ኤዲ) ሀብቱ መካሻ

(ዲዛይንና ጽሕፈት ሥራ አቤኔዘር ጽሕፈት ሥራ - መካኒሳ)